# አዲስቷ ኢትዮጵያ የአንድ ብሄር የበላይነትን ማስተናገድ ትችል ይሆን?

## 1. ህገ-መንግስቷ ምን ይላል?

አዲስቷ ኢትዮጵያ "የብሄር ብሄረሰቦች እስር ቤት" ተብላ ስትጠራበት ከነበረ የከፉ ዘመን ታሪኳ ተላቃ ሁሉም ብሄር፣ ብሄረሰብ እና ህዝቦቿ በአንድነት ቁመው ቋንቋቸው፣ ባህላቸው፣ ሃይማኖታቸው እና ወጋቸው እየተጠቀሙ እና እያሳደጉ ተከባብረው እና ተቻችለው የጋራ ጠላታቸው የሆነውን ድህነት ድባቅ ለመምታት እና ለማሸነፍ ብለውም የድሮ አለምን ያስደመመ ስልጣኔአቸውን ለማስመለስ የጦፈ የህዳሴ ጉዞ ጀምረው ሩቅ መጓዛቸውን ወዳጅ እና ጠላት፣ የቅርቡ እና የሩቁ እንዲሁም የውስጡ እና የውጩ እየመሰከረው ይገኛል፡፡

አዲስቷ ኢትዮጵያ "አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሃይማኖት እና አንድ ሃገር" ከሚለው የነገስታቱ እና የሰው በላው የወታደራዊ ስርዓቱ መርህ ተላቃ የእኩልነት፣ የመቻቻል፣ የአብሮ መኖር እና የብዝሃነትን መርሆ ዘርግታ መጓዝ ከጀመረች ውላ አድራለች፡፡ የዚች አገር የ1987 ዓ.ም ዘመናይ ህገ-መንግስትዋም እንዲህ የሚሉ ቁም ነገሮችን አስፍሮ የአንድ ብሄር የበላይነትን እንዳከተመለት በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

1- የኢፌድሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ አምስት ስለቋንቋ ሲያስቀምጥ በንኡስ አንቀፅ አንድ ላይ "ማናቸውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በእኩልነት የመንግስት እውቅና ይኖራቸዋል" ይላል፡፡ ወረድ ብሎ ንኡስ አንቀፅ ሶስት ደግሞ "የፌዴሬሽኑ አባሎች የየራሳቸውን የስራ ቋንቋ በህግ ይወስናሉ" በማለት የ"አንድ ቋንቋ" መርህ ላንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ማክተሙን አብስረዋል፡፡

2- "እንድ ሃይማኖት" ለሚለው ያረጀ ያፈጀ መርሆም አዲስቷ ኢትዮጵያ እያስተናገደች እንዳልሆነ በኢፌድሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ አስራ አንድ "የመንግስት እና የሃይማኖት መለያየት" በሚለው ርእስ አንቀፅ አንድ ላይ "መንግስት እና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው" አንቀፅ ሁለት ደግሞ "መንግስታዊ ሃይማኖት አይኖርም" ብሎ እቅጩን ነግሮናል፡፡

3- ሌላው አዲስቷ ኢትዮጵያ የአንድ ብሄር የበላይነት ዳግመኛ እንዳይመጣ የተከላከለችበት እና ከመጣም መፍትሄ ይሆናል ብላ ለህዝቦቿ እኩል ተጠቃሚነትና የስልጣን ባለቤትነት ዋስትና ይሆን ዘንድ በህገ-መንግስቱ በማያወላዳ መልኩ አስቀምጣለች፡፡ አንቀፅ ሰላሳ ዘጠኝ ላይ "የብሄሮች፣ ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች መብት" በሚለው ስር፡-

አንቀፅ አንድ - “ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ህዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው” ይላል፡፡ ቀጥሎም፡-

አንቀፅ ሁለት - “ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ህዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለፅ፣ የማዳበር እና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው” ይላል፡፡

እነዚህ ትላልቅ ቁም ነገሮች ወስደን አዲስቷን ኢትዮጵያ የአንድ ብሄር የበላይነትን ማስተናገድ እንደማትችል ነው እያመላከቱን የሚገኙት ወይስ እንደምትችል? መልሱ የአዲስቷን ኢትዮጵያ ህዳሴ ለሚፈልግ ንፁህ ልቦና ላለው አንባቢ ልተወው፡፡

“ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት አይጠፋም” እንደሚባለው ሁሉ ህገ-መንግስቱን ባግባቡ ያልተረዱ፣ የጓደኛ አሉባልታ እና የዘንድሮው “የፌስ ቡክ ጀግኖች” የነሸጣቸው አንባቢዎቼ ደጋግመው ህገ-መንግስቱን አይተው፣ አንብበው እና ተረድተው ህገ-መንግስቱን ለማክበር እና ለማስከበር እንዲቀሳቀሱም እስኪ ሌላ አስረጂ ላክል፡፡

4- የኢፌድሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ አርባ ስድስት “የፌዴራል ክልሎች” በሚለው ርእስ በንኡስ አንቀፅ አንድ ላይ “የፌዴራሉ መንግስት በክልሎች የተዋቀረ ነው” ይል እና በአንቀፅ አርባ ሰባት “የፌዴራል መንግስት አባላት” በሚል ርዕስ ስር ንኡስ አንቀፅ አራት ደግሞ “የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያ ሪፐብሊክ አባላት እኩል መብትና ስልጣን አላቸው” በማለት አንደኛው ክልል እላፊ ስልጣን እንደሌለው እና ሌላኛው ክልል ዝቅተኛ መብት እንደሌለው በግልፅ ተቀምጦ እናገኘዋለን፡፡

ስለዚህ አዲስቷ ኢትዮጵያ ህዝቦቿ የሚተዳደሩበት ህገ-መንግስት እንደ አፄዎቹ ዘመን ከካቧፓኑ ህገ-መንግስት ተገልብጦ እንደ ስጦታ የተበረከተላቸው ሳይሆን ህዝቦቿን የሚበጅ ብዝሃነቷን የሚያስተናግድ በህዝቦቿ ሙሉ ተሳትፎ እና ይሁንታ የፀደቀ ዘመን ተሻጋሪ ህገ-መንግስት ያላት እና በዛው እየተመራች እስከቀጠለች ድረስ ደግሞ የአንድ ብሄር ወይም ቡድን የበላይነትን የሚሸከም ጫንቃ እንደሌላት ህገ-መንግስቷ በጉልህ አስቀምጧል፡፡

**2.** የአዲስቷን ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታስ ምን ያሳያል?

እንደምናየው አዲስቷ ኢትዮጵያ በዘጠኝ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች እና በሁለት የከተማ መስተዳድሮች ተዋቅራ በልማት ጎዳና እየተራመደች ትገኛለች፡፡ ዛሬ በሁሉም ክልሎች ተንቀሳቅሰህ የሚነበቡ ለውጦች የኢትዮጵያ ህዝብ እድሉ ሲያገኝ ተአምር እንደሚሰራ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያዊያን የአንገዛም ባይነት ታሪካችን ጎላ ብሎ የሚታወቅ ቢሆንም የስልጣኔ ታሪካችንም አክሱም፣ አልነጃሺ፣ ላሊበላ፣ የፋሲለደስ ቤተ-መንግስት፣ ሃረር፣ ጅማ እና ሌሎች አካባቢዎችን ተዘዋውሮ ቋሚ አሻራዎቻችንን ላየ ሰው የኢትዮጵያ ስልጣኔ ከፍታው ምን ያህል ሆኖ እንደነበር መገመት ያስቸግረዋል አይባልም፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያዊያን ድህነትን ነበር አድርገው ወደ ቀድሞ የስልጣኔ ማማቸው ለመውጣት ብዙ ርቀት የመጓዛቸው ምስጢር ህገ-መንግስታዊ መብቶቻቸውን ተጠቅመው እልህ እና ቁጭት አንግበው መታገላቸው ብቻ እንደሆነ ሁኔታቸውን ተገንዝበህ መመስከር ይቻላል፡፡

የአሁኑ ጉዞ እንቅፋት የለውም ባይባልም እንቅፋቱ ግን እንደ ትላንትናው ስርዓቱ የወለዳቸው እንቅፋቶች አይደሉም፡፡ ምክንያቱም ስርዓቱ ራስን በራስ የማስተዳደር እና የመልማት ፀጋን አጓናፅፎናል እና፡፡ በአሁኗ ኢትዮጵያ እያንዳንዱ ክልል ያለውን ሃብት በአግባቡ አማጦ በመጠቀም ድህነትን ማሸነፍ የሚያስችለው ሙሉ ስልጣን በትግሉ አረጋግጧል፡፡ ህዝቡ የአገሩን፣ የክልሉን፣ የወረዳውን እና የቀበሌውን አስተዳዳሪዎቹ የመምረጥ፣ የመገምገም እና የማውረድ እንዲሁም በጀቱን የመቆጣጠር ባለሙሉ ስልጣን እንደሆነ ፈቅዶ እና መክሮ ያፀደቀው ህገ-መንግስቱ አስቀምጦለታል፡፡ የትላንቱን “ሲሾም ያልበላ…” የሚለውን አባባል ወርሰው ያቺን ውስን ሃብቷን ለመቀራመት የሚፈልጉ ወይም ተቀራምተው ህዝቡ ሊደርስባቸው ሲል የህዝብ ተቆርቋሪ መስለው የህዝቡን ደካማ ጎን ተጠቅመው የህዝቡን ርካሽ ተወዳጅነት ለማስቀረት እና ህዝብና መንግስትን በማላተም ማምለጫ ቀዳዳ የሚፈጥሩ ባለስልጣናት ግን አልጠፉም፡፡ እነዚህ የድሃውን ህዝብ ሃብት ተቀራምተው ያበጡ የህዝቡ መዥገሮች የሚፈጥሩት ቀዳዳ ግን የአዲስቷን ኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ የሚያቀጭጭ የጥፋት መንገድ መሆኑን በአገራችን በቅርቡ ተከስቶ የነበረውን ህውከት እና ግርግር ጉልህ ማሳያ ነው፡፡

በትረ ስልጣንን በነውጥ እና በውዥንብር ጨብጠው ከአንዳንድ የሃገራችን ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ወግነው እና የነሱ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆነው የአዲስቷን ኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ ወደ ኋላ ለመመለስ እየጣሩ የሚገኙ ሓይሎች አንዳንድ የኢህአዴግን ካባ አጥልቀው ኢህአዴግን ለማፍረስ ከሚተጉ ግለሰቦች ጋር በመቆራኘት “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” ከሚል ብሂል እየተነሱ ለዘመናት አብረው የኖሩ፣ ወልደው ተዋልደው፣ ቀደም ሲል የውጭ ወራሪዎችን በመመከት በቅርቡም የውስጥ አምባገነኑን ስርዓት ለመገርሰስ በተካሄደው መራራ ትግል እንደ አንድ ሰው ሆነው አብረው ተዋግተው በአንድ ጉድጓድ እየተቀበሩ አንድነታቸውን ያጠናከሩ የመጡ ህዝቦች ሓላፊነት በጎደለው መልኩ እርስ በርስ እንዲናቆሩ እና አንዱ ሌላኛውን በጠላትነት እንዲያይ የሚያስችል “የትግራይ የበላይነት አለ” እያሉ መርዛም ወሬ እየነዙ በህዝቦች መተላለቅ ትርፍ ለማትረፍ እየጣሩ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ለጥፋት የተሰባሰቡ ሓይሎች በበሬ ወለደ ውሸት ህዝቡን አናቁረው የስልጣን ጊዜአቸውን ለማራዘም እና ስልጣን ይዘው አገራችንን ለመበታተን እንቅልፍ አጥተው ላይ ታች ቢሉም የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ግን የአንድን ብሄር ወይም ቡድን የበላይነት ሊያስተናግድ የሚችል ስርዓት የለም፡፡ አሁንም እንዴት ላላችሁ መልሴን በምሳሌ አስደግፌ ላቅርብላችሁ እና ተከተሉኝ፡-

ምሳሌ አንድ፡- የክልሎችን ስልጣን በሚመለከት፡-

- አንድ ክልል በሌላኛው ክልል ላይ የክልሉን ስልጣን ተጋፍቶ እንደዚህ አድርግ አታድርግ የሚልበት ሁኔታ የለም፡፡ ለምሳሌ የትግራይ ክልላዊ መንግስት ህዝቡን አንቀሳቅሶ በጀቱን ባግባቡ ተጠቅሞ ህዝቡን የሚያረካ የልማት እና የመልካም አስተዳድር ተግባር ሲያከናውን አበጀህ! ተብሎ የሚወደሰው የክልሉ መንግስት ነው፡፡ በአንፃሩ የሚሰራውን እያዘፈ ማየት የሚገባውን ግድፈት ሳያይ የህዝቦችን ጥያቄ ኢ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚጥር ከሆነም የሚኮነነው የክልሉ መንግስት ነው፡፡ የክልሉ መንግስት "በክልሌ ፀረ-ዴሞክራያዊ ተግባር ለማቅጥቀጣቸው ምክንያት የሚሆነው በኦሮምያ ክልል ጠባብነት እና ሙስና ጎልተው በመውጣታቸው ነው፡፡ ወይም በአማራ ክልል የሚገኙ አንዳንድ ባለስልጣናት የአርማጭሆን መሬት ቸብችበው ከደለቡ በኋላ የፖሊስ ካቴና ሳይጎበኛቸው በፊት ወደ ትምክህት ጎራ ተቀላቅለው የትምክህት አስተሳሰብን እንዲገነግን በማድረጋቸው ነው" የሚል ከሆነ "የናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ" የሚለውን የአባቶች አባባል ተጠቅመህ ውስጥህን እይ ተብሎ መወቀስ አለበት ባይ ነኝ፡፡

እንዲሁም የአማራ ክልላዊ መንግስት ህዝቡን አደራጅቶ የአፈር እና ውሃ እቀባ ላይ ተረባርቦ ምርታማነትን ሲያሳድግ የልማት አርበኞች ተብለው የሚሸለሙት የክልሉ መንግስት እና ህዝቡ ናቸው፡፡ በአንፃሩ የክልሉን በጀት ወደ ልማት ከማዋል ይልቅ ከክልል ቢሮ ሃላፊ እስከ ከተማ ከንቲባ ላለው ተሿሚ አገልግሎት የሚውል **V8** የተባለው ዘመናዊ መኪና እየገዛ ሲያባክን እና ስልጣንን ለግል ምቾት ሲያውል ከርሞ እና "ለትግሬ አይፈራም ጎንደሬ" የሚለውን የትምክህተኛው ሓይል የወረደ እና የተሸነፈ አስፀያፊ አባባልን ወደ ህዝቡ እየረጨ ህዝብ ለህዝብ ለማፋጀት "ጦርነት ስለምንገጥም መሳርያ ግዙ እና ፍቃድ እናስታቅፋቹኋለን" እያለ የጎንደር አርሶ አደር እና ከተሜውን ላለው ብር ብድር ተመቻችቶለት የተወሰነ ብር ጨምሮ ባጃጅ ገዝቶ ድህነቱን እንዲቀርፍ ከመምራት ይልቅ በሃምሳ እና ስልሳ ሺህ ብር ክላሽ ገዝቶ እንዲታጠቅ እና የአገር የፀጥታ ጠንቅ እንዲሆን ሲያደርግ የቆየ አመራር ምን እየተደረገ ነው ያለው**?** ተብሎ በህዝብ ይሁን ያገባኛል በሚል ወገን ጥያቄ ሲቀርብለት "እኛ ለአማራ ህዝብ መብት መከበር በመቆማችን ልንወቀስ አይገባንም፣ የፌዴራል መንግስት የጦር መሳርያ ህግ ባለማውጣቱ ተቸግረናል፣ የወልቃይት የማንነት ጥያቄ ያንገበግበናል እንዲሁም የትግራይ የበላይነት ስላለ መቆም አለበት" እያለ የህዝብ ስሜት ኮርኩሮ ከተጠያቂነት ለማምለጥ የሚዘላብድ የክልል ባለስልጣን ሲገኝ ደግሞ ምንድ ነው ነገሩ ብለን "ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ" እንደሚባለው የራስ ችግር ወደ ሌላ ማላከክ እና ሰበብ መፍጠር አዋጭ እንዳልሆነ መነገር ይገባዋል፡፡

ባጠቀላይ በአሁኗ ኢትዮጵያ እያንዳንዱ ክልል እኩል መብትና ስልጣን እንዳለው በህገ-መንግስቱ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ህገ-መንግስታዊ መብቱን እና ስልጣኑን ተጠቅሞ በሰላም እና በልማት ሃዲድ የመጓዝ እና ያለመጓዝ ጉዳይ የራሱ የክልሉ እንጂ የሌላ የማንም እንዳልሆነ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ይደነግጋል፡፡ በአንድ ክልል ውድቀት ሌላ ክልል ወይም የፌዴራል መንግስት ተጠያቂ ወይም ተወቃሽ አይሆንም፡፡ እንዲሁም በአንድ ክልል እድገት ሌላ ክልል ወይም የፌዴራል መንግስቱ ተመስጋኝ አይሆንም ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የአንድ ብሄር ወይም ቡድን የበላይነት የሚኖርበት ምክንያት አይኖርም የሚለውን ያሳያል ማለት ነው፡፡

ምሳሌ ሁለት፡- እስኪ ስለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ስለፌዴሬሽን ምክር ቤት ደግሞ እንይ፡-

- ሌላው የአንድ ብሄር ወይም ቡድን የበላይነት አለ ወይስ የለም የሚለውን ለማየት ትንሽ ስለአዲስቷ ኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንስተን እንመልከት፡፡ የአሁኑ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደ ንጉሱ ዘመን በዘር ሃረጋቸው ተመርጠው ለንጉሱ ታማኝ የሆኑ ግለሰቦች የተሰባሰቡበት ሳይሆን የእያንዳንዱ ብሄር ፣ ብሄረሰብ እና ህዝብ ተወካዮች የተሰበሰቡበት እና የምክር ቤቱ መቀመጫም የህዝብ ብዛትን ማእከል ያደረገ እና አነስተኛ የህዝብ ብዛት ያላቸው ብሄረሰቦችንም ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ይታወቃል፡፡ ህገ-መንግስቱ የሚለውን ቃል በቃል ለማስቀመጥም፡-

- የህገ-መንግስቱ ምዕራፍ ስድስት አንቀፅ ሃምሳ ሶስት የፌዴራል መንግስት ምክር ቤቶች በሚል ርእስ ላይ፡-

  "የፌዴራሉ መንግስት ሁለት ምክር ቤቶች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ናቸው" ይላል፡፡

  እንዲሁም በክፍል አንድ አንቀፅ ሀምሳ አራት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በሚለው ርእሱ ላይ ንኡስ አንቀፅ ሶስት ደግሞ ምን እንደሚል እንመልከት፡-

  "የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር የህዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው አናሳ ብሄረሰቦች እና ህዝቦችን ቁጥር መሰረት በማድረግ ከአምስት መቶ ሓምሳ የማይበልጥ ሆኖ ከዚህ ውስጥ አናሳ ብሄረሰቦች ከሃያ የማያንስ መቀመጫ ይኖራቸዋል፡፡" ይላል፡፡

  ከዚህ በመነሳት ትልቁ የሃገራችን ስልጣን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደተሰጠ ህገ-መንግስቱ ያስቀምጣል ማለት ነው፡፡ ወደነዚህ ምክር ቤቶች የሚገቡም በአንድ ብሄር ወይም ቡድን ተመርጠው እንዳልሆነም ህገ-መንግስቱ በማያወላዳ መልኩ አስቀምጧል፡፡

- የነዚህ ምክር ቤቶች ስልጣንስ ለአንድ ብሄር ወይም ቡድን ልእልና የተጋለጡ ናቸው አይደሉም የሚለውን ለማየትም ከእያንዳንዳቸው ምክር ቤቶች ስልጣን ወስደን አንዳንዶች እንመልከት፡- አንቀፅ ሀምሳ አምስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስልጣን እና ተግባር ከሚለው ውስጥ ንኡስ አንቀፅ አስራ አንድ ላይ እንዲህ ይላል፡-

  "ለፌዴራል መንግስት በተካለለው የገቢ ምንጭ ክልል ግብርና ታክስ ይጥላል፡፡ የፌዴራል መንግስት በጀት ያፀድቃል፡፡"ይላል፡፡

  ወረድ ብሎም በክፍል ሁለት አንቀፅ ስልሳ አንድ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት በሚል ርእስ ንኡስ አንቀፅ ሁለት ላይ፡-

  "እያንዳንዱ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ህዝብ ቢያንስ አንድ ተወካይ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የብሄር ወይም ብሄረሰቡ አንድ ሚልዮን ህዝብ አንድ ተጨማሪ ወኪል ይኖረዋል፡፡"

በማለት የፌዴሬሽን ምክር ቤትም በአንድ ቡድን ወይም ብሄር እንዳልተዋቀረ ያስረዳናል፡፡ የዚህ ምክር ቤት ስልጣን እና ተግባር በሚገልፀው አንቀፅ ስልሳ ሁለት ንኡስ አንቀፅ ሰባት ደግሞ እንዲህ ይለናል፡፡

> "የክልሎች እና የፌዴራሉ መንግስት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ለክልሎች ድጎማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል፡፡" ብሎ ያስቀምጣል፡፡

ስለዚህ የአገራችንን የስልጣን ነባራዊ ሁኔታ ይህንን ነው የሚመስለው፡፡ ትምክህተኞች "ህገ-መንግስቱ እኮ ህገ-ኦራዊት ነው" ብለው ሲያንቋሽሹት እንደ ትላንቱ እነሱ ደርሰው ስላልሰጡን እና እንደ ሰው እንኳ ሲታዩ ያልነበሩ የአገራችን ብሄር፣ ብሄረሰብ እና ህዝቦች ተፈቃቅደው፣ መክረው እና ዘክረው ስላፀደቁት እንጂ ህገ-መንግስቱ የትግራይን የበላይነት ስለሚያሳይ አይደለም፡፡

በሁሉም ምክር ቤቶቻችን ያለው የአወካከል ስርዓት ህገ-መንግስቱን ጠቅሼ ለማሳየት ሞክሬአለሁኝ፡፡ ምናልባት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያለው ተመራጭ ኢህአዴግን ወክሎ የገባ ነው ሲባል ሁሉም የትግራይ ተወላጅ የሚመስለው እንዳይኖርም እስኪ ኢህአዴግ የሚያስተዳድራቸው አራቱ የኦሮምያ፣ የአማራ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል እና የትግራይ ክልል የመቀመጫ ወንበር ብዛትን እንይ፡-

- የኦሮምያ ክልል 178 ተወካዮችን የሚይዝ መቀመጫ ወንበር፣
- የአማራ ክልል 138 ተወካዮችን የሚይዝ መቀመጫ ወንበር፣
- የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል 123 ተወካዮችን የሚይዝ መቀመጫ ወንበር እና
- የትግራይ ክልል 38 ተወካዮችን የሚይዝ መቀመጫ ወንበር አሉዋቸው፡፡

የሌሎች ክልሎች እና የሁለቱ ከተማ አስተዳደሮችም እንደየ ህዝብ ብዛታቸው የመቀመጫ ወንበር አላቸው ማለት ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው የምክር ቤት የመቀመጫ ወንበር ብዛት ስሌት ነው እንግዲህ የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ እና ህዝቦች አገራቸውን እየመሩ የሚገኙት፡፡

ይህ የተከበረው የአገራችን ምክር ቤት የመቀመጫ ወንበር ብዛት የያዘው ብሄር ወይም ክልል ስናይ ምናልባት የዋሆች የኦሮሞ እና የአማራ ህዝብን ወክለው በምክር ቤቱ የሚገኙ ብዛት ስላላቸው የኦሮሞ ወይም የአማራ የበላይነት አለ ብለው መናገር ይችሉ ነበር፡፡ ግን የተባለው 38 የምክር ቤት መቀመጫ የያዘ የትግራይ ህዝብን ነው የበላይነቱ እያረጋገጠ ነው ብለው ሲያጠቁሩት የሚሰሙ፡፡ ምናልባት የዳር ድንበራችንን ጥበቃ እያካሄደ የልማቱ እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ግንባታ አለምንም አደናቃፊ ሓይል እንዲቀላጠፍ ከማድረጉ ባሻገር በአፍሪካ ሰላም ማስከበር ሂደትም ጉልህ ሚና እየተጫወተ ያለው የመከላከያ ሀይላችን ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች እና አገራችንን ከሽብር እና ከቀለም አብዮተኞች ሴራ እየተከላከሉ አለም በሽብርተኝነት እየተናወጠ ባለበት ወቅት ኢትዮጵያ ግን ሰላሟን ጠብቃ የህዳሴ ጉዞዋን ያለእንከን እንድታስቀጠል እያደረጉ

ከሚገኙ ሌሎች የፀጥታ ሓይሎቻችን ውስጥ የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች በኢፌድሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስውር መቀመጫ ስላላቸው የአገሪቱን በጀት እነሱ ነው የሚቆጣጠሩት እና የሚያስተዳድሩት ሊሉን እንደሆነ እንጃ እንጂ መሬት ላይ የሚታይ እውነታ ግን የትግራይ የበላይነት የሚያስብል ይቅር እና የምክር ቤቱ ብዙ መቀመጫ ያላቸው የኦሮሞ እና የአማራ የበላይነት አለ የሚያስብልም የለም፡፡ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ሳይሸራረፍ እስከ ቀጠለ ድረስም የማንም ብሄር ወይም ቡድን የበላይነት ሊኖር አይችልም፡፡

## 3. የህወሓት የበላይነት እንዳይኖር ህወሓት የተከፈለው መስዋእትነት

የትግራይ ህዝብ እና መሪ ድርጅቱ ህወሓት አሁን ለምናያት አዲስቷ ኢትዮጵያ ለመፍጠር የከፈሉት ሁሉን አቀፍ መስዋእትነት የኢትዮጵያ ህዝብ ተገቢውን ክብር ይሰጠዋል ብዬ እገምታለሁ፡፡ የትግራይ ህዝብ እና መሪ ድራጅቱ ህወሓትም የከፈለው መስዋእትነት መከፈል የነበረበት ታሪካዊ መስዋእትነት ነው ብሎ አምኖ እና ተቀብሎ በመስዋእትነቱ የተጎናፀፈው ዲሞክራሲያዊ መብት ተጠቅሞ የክልሉን ድህነት በመዋጋት አገራዊ ግዴታውን ወደ መወጣት ነው ያተኮረው እንጂ ካሳ ይገባኛል እና እላፊ ጥቅም ይሰጠኝ አላለም፡፡ ከመስዋእትነት የቀሩ ጀግኖች ልጆቹ የመንግስት ስልጣን ይዘው ይጠቀሙ ሳይሆን ያለው ለሁላችን የምትመስል አዲስቷ ኢትዮጵያ ለመገንባት አሁንም ሌላ መስዋእትነት መከፈል ታሪካዊ ግዴታየ ነው ብሎ ተቀብሎ ተጨማሪ ዕዳ ለመከፈል ነው የተገደደው፡፡ እንዴት ብላችሁ የጠየቃችሁኝ እንደሆነ ደግሞ ላስረዳችሁ፡፡

- ደርግ ከትግራይ ተጠራርጎ ወጥቶ ወደ መሃል አገር እየሸከፈ በመጣ ወቅት በሙቶዎች የሚቆጠሩ ነባር እና በክፍለ ህዝብ ሰራ ሲሰሩ የነበሩ የህወሓት ካድሬዎች የኢህአዴግ ሰራዊት ነፃ ባወጣቸው አካባቢዎች የሰራዊቱን እግር እየተከተሉ አደራጅም ተዋጊም እየሆኑ እህት ድርጅቶች የያኔ ኢህዴን የአሁኑ ብአዴንን፣ ኦህዴድን ኋላም ደኢህዴንን በማገዝ ተግባር ተሰማርተው ህዝቡን እና ኢህአዴግን በማገናኘት የማይተካ ሚና የተጫወቱ እና አገሪቱን በማረጋጋት ረገድም ከፍተኛ አስተዋፅኦ የነበራቸው የህወሓት ታጋዮች በየተመደቡበት አካባቢ የነበረው ህዝብ “ትታችሁን አትሄዱም፣ ያ ሁሉ መከራ አልፋችሁ እኛን ከመቀመቅ እንድንወጣ አንቅታችሁን እና አደራጅታችሁን ስታበቁ እንደ ልጆቻችን እዚሁ ድረን እና ሓላፊነት ሰጥተን ትመሩናላችሁ እንጂ ወደ ትግራይ እማ አትመለሱም” ብሎ እየተማፀነም ጭምር መሪ ድርጅቱ ህወሓት ግን “ለትግል ተሰማርታችሁ አኩሪ ውጤት አስመዝግባችኋል፡፡ ተተኪ ሃይልም አፍርታችኋል፡፡ አነሳሳችንም እንደ ቀደምቶቹ ነፍጠኞች በገባንበት ልንቀር እና ህዝቡን በሞግዚት ልናስተዳድር ስላልነበረ እና ባህሪያችን ስለማይፈቅድ ሁላችሁም ወደ ክልላችሁ ተመለሱ እና ተመድባችሁ ህዝባችሁን ትመራላችሁ” ብሎ ከ1981 ዓ.ም እስከ 1985 ዓ.ም ከትግራይ ውጭ በካድሬነት ተመድቦ እየሰራ የነበረ ታጋይ እንዲመለስ አድርጓል፡፡ ይህ አቋም የአንድ ብሄር ወይም ቡድን የበላይነት እንዳይኖር ከሚታገል ድርጅት የመነጨ አቋም እና የተተገበረ ድርጊት መሆኑን ያሳያል፡፡

- ሌላኛው ህወሓት ህብረ-ብሄራዊ ስርዓቱን ለማጠናከር ከከፈላቸው መስዋእትነቶች የሚያሳይ ትልቅ አብነትም ላክልላችሁ፡፡ እንደሚታወቀው የደርግ ስርዓት ከተገረሰሰ በኋላ የኢህአዴግ ሰራዊት የሽግግር መንግስት ሰራዊት ሆኖ እንዲቀጥል ስምምነት ተደርሶ ነበር፡፡ በታሪክ አጋጣሚ ደግሞ በኢህአዴግ ሰራዊት ውስጥ አብላጫ ቁጥር የያዘው የህወሓት ታጋይ ነበር፡፡ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ለማመን የሚያስቸግሩ ጀግንነት እየፈፀመ ሰው በላው ወታደራዊ ስርዓትን የገረሰሰ እና ኋላም የአገሪቱን የሰላም እና ማረጋጋት ስራን በአግባቡ የተወጣ ሓይል እንደ ሰራዊት ተቀብለህ፣ ክብር ሰጥተህ እና ደመወዝ ተክለህ ማስቀጠል ነበር

የሚጠበቀው፡፡ ሆኖም ግን ህወሓት እና አመራሩ አዲስቷን ኢትዮጵያ ስንገነባ አገሪቷን የሚመስል ጦር እና የመከላከያ ሰራዊት መገንባት አለብን ብሎ በፅናት አምኖ ብዙዎች በትጥቅ ትግል ወደ ስልጣን የመጡ የአፍሪካ አገሮች ያላደረጉት ሌላ መስዋእትነት ለመክፈል ተገደደ፡፡ ሰራዊቱን እና ህዝቡን በማሳመን ያ ዛሬ ነገ ደመወዝ ተከፋይ ሆኜ ቤተሰቤን መርዳት እጀምራለሁ እያለ የመጣ ጀግና "አዲስቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት ስትል አሁንም ተመልምለህ እና ተቀንሰህ ወደ እርሻህ ትሄዳለህ" ተብሎ በአስር ሺዎች የሚቆጠር የህወሓት ታጋይ ከተራ አባልነት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ጦር አመራር የነበረውንም ባካተተ መልኩ እንዲቀነስ ተደርጎ ነበር፡፡ ይህም አልበቃም፡፡ የአዲስቷን ኢትዮጵያ የመከላከያ አባል ሆነህ ትቀጥላለህ የተባለ የህወሓት ታጋይም የአመራርነት ቦታህ ለሌሎች የብሄር ብሄረሰብ ተወላጅ አባላት ትለቃህ በሚል ከነበረበት የሓላፊነት ደረጃ ሁለት ሁለት ደረጃ እንዲቀነስ እና ሌሎች በተለይ በወቅቱ የሰራዊቱ አባላት የነበሩ የያኔው ኢህዴን የአሁኑ ብአዴን እና የኦህዴድ ታጋዮች ግን በያዙት የአመራርነት ደረጃ እና ከዛ በላይ እያገኙ እንዲቀጥሉ የተደረገበት ሁኔታ ነበር፡፡

ህወሓት ይህ አይነቱ መራራ ውሳኔ ሲወስን እና ውሳኔውን ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ ወደኋላ ያላለው የትግራይ ህዝብ እና ታጋይ ልጆቹ "ድሮውንም የታገልነው በእኩልነት ሰርተን የምንኖርባት ኢትዮጵያን ለማምጣት እንጂ እንደቀድሞዎቹ እንሆናለን ብለን አልነበረም" በሚል የአላማ ፅናት ነበረ መራራ ውሳኔውን አለማንገራገር የተቀበሉት፡፡ ይህ ትልቅ የህወሓት እና የትግራይ ህዝብ መስዋእትነት የሚያሳየው ምን ያህል የአገር ፍቅር እንደነበራቸው እና የአንድ ብሄር ልእልናን አውግዘው ለአዲስቷ ኢትዮጵያ ግንባታ ምን ያህል ቁርጠኞች መሆናቸውን ነው፡፡ ታድያ ይህንን ኩሩ እና ለቆመለት አላማ መስዋእት ለመሆን ወደኋላ የማይል ህዝብ እና ድርጅት አዲስቷን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ላበረከተው ጉልህ አስተዋፅኦ "እናመሰግንሃለን" የሚለውን ክብር መስጠት ነው የሚገባው ወይስ "የትግራይ የበላይነት" በሚል የትምክህተኞች እና ጠባቦች ጩኸት ማደንቆር እና የጥቃት ኢላማ ማድረግ? አሁንም መልሱ ለአንባቢ ይሁን ብያለሁ፡፡

- ሶስተኛ አብነትም አለኝ የህወሓት አመራር "ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረሰብ አገር ናት፡፡ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ ከገቡበት አዘቅት ለመውጣት መታገያ መስመር ካገኙ ታግለው አስከፊውን ስርዓት መገርሰስ እና አዲስቷን ኢትዮጵያ መፍጠር ይችላሉ" በሚል ዴሞክራት ሓይሎችን አሰባስቦ ኢህአዴግ የሚባለውን ድርጅት በመመስረት አሁን ላለነው ደረጃ እንድንደርስ የማይተካ ሚና ነበረው የሚል እምነት አለኝ፡፡ እነዚህ አመራሮች እንደ ሌሎች "አንጋፋ የኢትዮጵያ ድርጅቶች" እየተባሉ የሚቆለጳጰሱት የአውሮፓ እና አሜሪካን ኑሮ ሳያማልላቸው የህዝባቸውን ችግር እና ሰቆቃ እያነበቡ እና በዛው እያለፉ ታግለው፣ አታግለው፣ በመውደቅ እና መነሳት ተምረው፣ አገራቸውን እና ህዝባቸውን የሚመስል ፖሊሲ በመንደፍ ጥበብ በተሞላበት አኳኋን የደርግን ስርዓት ተገርስሶ አዲስቷን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ በተደረገው እና እየተደረገ ባለው ትግልም ሚናቸው ቀላል እንዳልነበር እና እንዳልሆነ ለማንም ግልፅ ይመስለኛል፡፡

እነዚህ አመራሮች ግን ደርግ እንደ ወደቀ ሁሉንም የስልጣን ቦታ ተከፋፍለን ለብቻችን እንያዘው አላሉም፡፡ "ከሚገባን በላይ ስልጣን የምንይዝበት ጉዳይ የለም፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ እስከሚጎለብት ድረስ ኢህአዴግ በሚወስነው መሰረት የተወሰኑ የስልጣን ቦታዎችን ካልሆነ በስተቀር እንደየ አመጣጣችን እና ባለን አቅም መሰረት ስልጣን እንያዝ ካልን የተመኘናትን አዲስቷን ኢትዮጵያ እውን አትሆንም" በሚል መርህ በተለይ ከሽግግር መንግሰቱ ማብቃት ማግስት አመራሮቹን የማሸጋሸግ ስራ መስራቱ የትላንት ሓቅ ነው፡፡ እነማን እና እንዴት ካላችሁኝ ደግሞ የተወሰኑትን ላስታውሳችሁ፡፡

ሀ. ባላቸው የግልፀኝነት ጥንካሬ፣ የዳበረ ፖለቲካዊ አቅም እና በራስ የመተማመን ሁኔታቸው በበርካታ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ተወዳጅነት እና ታዋቂነትን ያተረፉ አቦይ ስብሓት የማያውቅ የለም ብዬ እገምታለሁ፡፡ አቦይ ስብሓት ነጋ ከትጥቅ ትግሉ በፊት አንደኛ ዲግሪያቸውን ይዘው በአስተማሪነት እና በርእሰ መምህርነት ህዝባቸውን አገልግለው ነው የትጥቅ ትግሉን የተቀላቀሉት፡፡ የህወሓት መስራች እና ከአስር ዓመት በላይ ህወሓትን በሊቀ መንበርነት የመሩ ታጋይና የታጋዮች አባት ናቸው፡፡

ታድያ ለእኚህ አንጋፋ መሪ የሚሆን የመንግስት ቱባ ስልጣን ታጥቶ ይሆን እስከ አሁን የመንግስት ባለስልጣን ያልሆኑት? በትግል እና በአመራር ዘመናቸው ያካበቱት እውቀት ይዘው አንድ የሚኒስትር መ/ቤት ቢይዙ ኖሮ ለአዲስቷ ኢትዮጵያ በጠቀሙ ነበር፡፡ ግን ድርጅታቸው እና ራሳቸው "አዲስቷ ኢትዮጵያ የምትጠቀመው ሁላችን የመንግስት ስልጣን ስንይዝ ሳይሆን ለሌሎች ስልጣን ስናካፍል እና የአንድ ብሄር የበላይነት እንዳይኖር መታገላችንን በተግባር ስናሳይ ነው" የሚል ፅኑ አቋም በመያዝ ደርግ ከወደቀ ጀምሮ እስከ አሁን ወደ የመንግስት ስልጣን የሚባል ሳይጠጉ እንደማንኛውም ታጋይ ድርጅታቸው በመደባቸው ሌላ ድርጅታዊ ስራ ተመድበው እየታገሉ እና እያገለገሉ ቆይተው አመሻሽ ላይ ደግሞ እንደምንረዳው የአንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ዳይሬክተር ሆነው እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ ለአዲስቷ ኢትዮጵያ ሰላም፣ ደህንነት እና ልማት እየተጉ ይገኛሉ፡፡

ለ. ሌላው የህወሓት መስራች እና የህወሓት የፖለቲካ ዘርፍ ሓላፊ የነበሩ እና አሁንም የመንግስት የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ዋና ዳይሬክተር ሆነው እየሰሩ የሚገኙ አቶ አባይ ፀሀዬንም እናውቃቸዋለን የሚል አለኝ፡፡ እኚህ አንጋፋ ታጋይ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የታላቁ መሪያችን የአቶ መለስ የበላይ ሓላፊ ሆነው የህወሓት የውስጥ ድርጅት ፖለቲካ ሓላፊ በመሆን እንደ ሌሎች የትግል ጓደኞቻቸው ሓላፊነታቸውና ግዴታቸውን የተወጡ አመራር ናቸው፡፡

አቶ አባይም ብዝሓነቷን የምታስተናግድ ኢትዮጵያ ትመሰረት ዘንድ የሽግግር መንግስቱ በሚያበቃበት ወቅት "በጦርነት እና በድርቅ የተጎዳችውን ትግራይ እንድታገግም ያለህን የአመራር ብቃት እና ጥበብ ተጠቅመህ የተቀናጀ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ለመስራት እንደገና ወደ ትግራይ በርሃዎች ዝመት" ተብለው በወቅቱ Sustainable Agricultural Rehabilitation of Tigry (SART) ተብሎ ተቋቁሞ በነበረ የምግባረ ሰናይ ድርጅት ስራ አስኪያጅ ሆነው ተመድበው ሌላ መታገያ ክንፍ ተሰጥቶአቸው እንዲሰሩ ሲመደቡ የአቶ አባይ የአመራር ጥበብ ለአንድ የመንግስት ሚኒስትር መ/ቤት ለመምራት የሚመጥን ስላልነበረ አይመስለኝም፡፡

ሐ. በትግል ውስጥ ውጣ ውረድ ስላለ የኋላ ኋላ ከትግሉ ሃዲድ አፈንግጠው ወጥተው አሁን በተቃዋሚ ጎራ የሚገኙ ቢሆንም ያኔ በአፍሪካ ተወዳዳሪ ላልነበረው ዘመናዊ የደርግ ሰራዊት አራት ወር ባልሞላ ጊዜ አስገራሚ በሆነ ጀግንነት እና ፍጥነት ፍርክስክሱን እንዲወጣ ያደረገው የኢህአዴግ ሰራዊት በአዛዥነት ሲመሩ የነበሩ እና በሽግግሩ ወቅትም የመከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር ሆነው ያገለገሉ አቶ ስየ አብርሃ ነበሩ፡፡ በወቅቱም አቶ ስየ የድርጅታቸውን መርህ ተቀብለው የመከላከያ ሚኒስቴርነታቸውን ቦታ ለትግል ጓዳቸው ለብአዴኑ ለአቶ ተፈራ ዋልዋ አስረክበው የንግድ ኩባንዎችን እንዲመሩ ተመድበው እንደነበረ የትላንት ትዝታ ነው፡፡ ታድያ አቶ ስየ የአዲስቷን ኢትዮጵያ ህብረ ብሄራዊ ጦር እንዲደራጅ አድርገው ሲያበቁ አሰበውት ወደማያውቁት ወደ ንግዱ አለም ሲመደቡ እና ምድቡንም በፀጋ ተቀብለው ሲሄዱ ለምን ይሆን?

"እውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም" ካልሆነ በስተቀር የአቶ ስዩ ከጦር አዛዥነት ወደ ንግድ ኩባንያ መሪነት መመደብ ምክንያትም ያው እንደ ጓደኞቻቸው የታገሉበትን አላማ የአንድ ብሄር ወይም ቡድን የበላይነቱን የሚያረጋግጥባት ኢትዮጵያን መገንባት ሳይሆን ኢትዮጵያዊያንን የምትመስል ልዩነቷ ውበቷ እንደሆነ የምታስመሰክር አገር ማነፅ መሆኑን ጠንቅቀው ስላወቁ እና በተግባርም መግለፅ ስለፈለጉ ይመስለኛል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ የጠቃቀስኩዋቸው ውስን አብነቶች ብዙ ዘመን ያላስቆጠሩ የትናንትናዎቹ ሓቆች ስለሆኑ በቀላሉ ሊረጋገጡ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በላይም ሊዳብሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ሓቆች ደግሞ ህወሓት በኢትዮጵያ የአንድ ብሄር ወይም ቡድን የበላይነት እንዳይኖር ታግሏል የሚለውን ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን ህወሓት ራሱ በታሪክ አጋጣሚ በኢትዮጵያ የለውጥ ጉዞ ላይ የነበረውን ከፍታ ተጠቅሞ የበላይ እንዳይሆን በተግባር የከፈለው ፈርጀ ብዙ መስዋእትነትን የሚያሳዩ ሓቆች ናቸው፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያዊያን የህዳሴ ጉዞ እውን እንዲሆን የሚሻ ዜጋ ይህ በየጊዜው ብልጭ ድርግም እያለ የሚገኘው "የትግራይ የበላይነት" የሚለውን የፀረ-ኢትዮጵያ ሓይሎች ሴራ በጥንቃቄ ተገንዝቦ በቃ! እንዲለው ይገባል ባይ ነኝ፡፡ የትግራይ የበላይነት አለ እያሉ የሚጮሁ ሓይሎች ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ መግቢያ ልትሆነን ትችላለች ብለው አልመው ስለሆነ "አያ ጅቦ በማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ" እንደተባለው ነውና አይሳካላችሁም ብሎ እቅጩን በመንገር በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነቱን አጠናክሮ የማይቀረውን የኢትዮጵያ ህዳሴን ያብስር፡፡

የአሁኗ ኢትዮጵያ የአንድ ብሄር ወይም ቡድን የበላይነት የሚታይባት እንዳልሆነ ሌላው ይቅርና እነዛ ባህር ማዶ በሞቀ የፈረንጅ ቪላ ተቀምጠው በመሬት የሌለውን ጦር በፌስ ቡክ አዝምተው ድሃውን እና ግንፍሉን ወጣት በውዥንብር እንደ ቢራቢሮ ወደ እሳት እየከተቱት የሚገኙትም ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ኢትዮጵያም ከዚህ በኋላ የሚኖራት አማራጭ ሁለት እንደሆነ ኢትዮጵያዊያን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ምርጫውም፡-

- አንደኛው እና ተመራጩ ብዝሃነታችንን ያስተናገደ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ተንከባክቦ የአንድ ብሄር ወይም ቡድን የበላይነት የማይታይባት የአዲስቷን ኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ አጠናክሮ የበለፀገች እና ድህነትን አሸንፋ ፈርጣማ አገር ሆና መቀጠል ሲሆን ሁለተኛው እና የማይመረጠው ደግሞ በህውከት እና በግርግር ህገ-መንግስታዊ ስርዓቷ ፈራርሶ የህዝቦች የእርስ በእርስ እልቂት እና የመበታተን ምርጫ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው ምርጫ እንደማንመርጥ አልጠራጠርም፡፡ ስለዚህ "ጦር ከፈታው የፌስ ቡክ ወሬ የፈታው" ከሚለው  አባባል ይሰውረን እያልኩኝ ልሰናበት ቸር ይግጠመን፡፡

አልአሚን አማን

**25/05/2009** ዓ.ም

**agerbegara legara@gmil.com**